# የኢትዮጵያ ወላጆች የዘረኝነት ገጠመኞች

ከዚህ በታች [Best Starts for Kids (BSK)] የተሰኘው ተቋም፣ በ 2019 [BSK] የተደረገውን ከዘረኝነት ጋር የተያያዙ የሰባት ጥያቄዎች የጤና ዳሰሳ ጥናት ውጤቶችን፣ እና እነዚህን የዳሰሳ ጥናት ውጤቶች ማህብረተሰባቸውን ወክለው የገመገሙትን የቤተሰቦች ግብረመልስ እና አስተያየቶችን ያካፍላል፡፡ በ10 BIPOC ማህበረሰቦች ውስጥ የተካተቱት ቤተሰቦች በሁሉም የሕይወት ዘርፋቸው ላይ በተለያየ ደረጃ የዘረኝነት ተጽዕኖ ገጥሟቸዋል፡፡ ቤተሰቦቹ ዘረኝነት በ [BSK] የጤና ዳሰሳ ውስጥ እምብዛም እንዳልተዘገበ ተናግረዋል፡፡ ቤተሰቦች በአደባባይ እና በሙያዊ ቦታዎች ላይ የዘረኝነት ጥቃቶች/ተጽዕኖዎች ደርስባቸዋል፡፡ ከአብዛኞቹ ማህበረሰቦች የተውጣጡ ቤተሰቦች በልጃቸው ትምህርት ቤት ውስጥ የዘረኝነት ተጽዕኖዎች የተለመዱ መሆናቸውን ገልፀዋል፣ እንዲሁም አብዛኛዎቹ ማህበረሰቦች በጤና አጠባበቅ ስርዓት ውስጥ የዘረኝነት ክስተቶች እንዳሉ ገልፀዋል፡፡ ስለ [community café] ግኝቶች የበለጠ መረጃ ለማግኘት እባክዎ ሙሉውን የ [Community Café Collaborative] ዘገባን (በእንግሊዘኛ ብቻ የቀረበ ) ይመልከቱ፤ [https://bit.ly/3pMbzgf]



## ከ [Community Café] ውይይት ዋና ዋና ግንዛቤዎች እና ገጽታዎች፡-

የኢትዮጵያዊያን ማህበረሰብ፣ አብዛኛዎቹ ስደተኞች፣ በየቀኑ የዘረኝነት ጥቃቶች ይደርስባቸዋል፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎቹ በልጆቻቸው ትምህርት ቤት፣ በሥራ ቦታ፣ በሕዝብ ማመላለሻ እና በሕክምና አገልግሎት መስጫ እንዲሁም በተለያዩ የሕይወት መገልገያ ስፍራዎች ላይ መድልዎ እንደሚደርስባቸው ተናግረዋል፡፡ ብዙዎች በቆዳቸው ቀለም እና በቋንቋ ዘይቤአቸው ምክንያት ተጽዕኖ እንደደረሰባቸው ተናግረዋል፡፡

**38%**
**ኢትዮጵያውያን ወላጆች የዘረኝነት ጥቃቶች/ተጽዕኖ እንዳጋጠማቸው ተናግረዋል፡፡**

**በየእለቱ የዘረኝነት ጥቃቶች/ተጽዕኖ ከገጠማቸው ኢትዮጵያውያን ወላጆች መካከል፡-**

**58%** የሕክምና እንክብካቤ በሚያገኙበት ጊዜ

**62%** በልጆች እንቅስቃሴዎች ማዕከላት ላይ

**43%** በልጆች ትምህርት ቤት ውስጥ

በሥራ ቦታ፣ በመገበያያ ቦታዎች፣ በሕዝባዊ ቦታዎች እና በሌሎች በተለመዱ ስፈራዎች ላይ፡፡

**106**
ኢትዮጵያውያን ወላጆች ጥናታዊ ዳሰሳውን የወሰዱት በ2019 ላይ ነው፡፡

> “በፊት ለፊት በኩል ያለውን የቤቴን ግቢ በመጥረግ ላይ እያለሁ፣ አንድ ነጭ ሰውዬ፣ የቤቱን ባለቤት ልትጠሪልኝ ትችያለሽ? ብሎ ጠየቀኝ፡፡ እሱ የገመተው የቤት ሰራተኛ እንደሆንኩ ነበር፣ ነገር ግን ቤቴ እንደሆነ ነገርኩት፡፡”
> - ኢትዮጵያዊ [Community Café] ተሳታፊ

> “ልብስ ልገዛ ሄጄ፣ ልብሶች እየመረጥኩኝ ሳለ፣ ሻጯ መጥታ ሁሉንም ልብሶች መንካት እንዳቆም ነገረችኝ፡፡ ዝም ብዬ አጣጠፍኳቸው፡፡ ልገዛ ነው የመጣሁት አልኳት፡፡ እሷ የገመተችው የሚሸጡትን የብራንድ አልባሳት ለመግዛት አቅም የላትም ብላ ነው፡፡”
> - ኢትዮጵያዊ [Community Café] ተሳታፊ

> “ልጆቼ ትምህርት ቤት ሲገቡ፣ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርት እንደሚያስፈልጋቸው ተነግሮኝ ነበር፤ ነገር ግን ልጆቼ እዚህ ሀገር ነው የተወለዱት እና እንግሊዘኛ ቋንቋ በደንብ ይናገሩ ነበረ፡፡”
> - ኢትዮጵያዊ [Community Café] ተሳታፊ

King County

Best Starts for KIDS



ምስል፡ በቴዎድሮስ አየለ

**ማስታወሻዎች ፡-** የኢትዮጵያዊ [community café] ውይይት የተደረገው በአማርኛ ነበር፡፡
ኢትዮጵያውያን ወላጆች፣ በዳሰሳ ጥናቱ ላይ የኢትዮጵያን ዘር/ብሔር ቡድን የመረጡ ወላጆችን ይገልጻል፡፡ ብዙ ዘር ያላቸው ሰዎች በመረጡት በእያንዳንዱ ምድብ ውስጥ ይንፀባርቃሉ፡፡ ለምሳሌ፣ በዳሰሳ ጥናቱ ላይ ቬትናሚዝን እና ኢትዮጵያዊያንን የመረጡ ወላጅ ምላሾቻቸው በሁለቱም በቬትናሚዝ እና በኢትዮጵያውያን ውጤቶች ላይ ይቆጠራል፡፡
ፎቶግራፎቹ ከኢትዮጵያውያን ማህበረሰብ አባላት በልግስና የቀረቡ ናቸው፡፡ የጥበብ ስራው የሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ ነው፡፡